# የኢትዮጵያና የሱዳንን የጋራ ድንበር በተመለከተ የተሠጠ መግለጫ፣

አንዳንድ የመገናኛ ብዙሃን እና ኃላፊነት የጐደላቸው አካላት የኢትዮጵያ መንግሥት መሬት ቆርሶ ለሱዳን ሰጥቷል የሚል እጅግ አፀያፊ አሉባልታ በተለያዩ ጊዜያት ሲያናፍሱ ቆይተዋል:: ለእንደዚህ አይነት መሠረተ ቢስ አሉባልታዎች በየጊዜው ምላሽ መስጠት አላስፈላጊ ከመሆኑ ሌላ የድንበር ጉዳይ በባህሪው ጥንቃቄን ስለሚጠይቅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ ከመስጠት ተቆጥቦ ቆይቷል። እንደሚታወቀው ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ጠባብ የፖለቲካ አጀንዳ ለማራመድ የሚሹ አካላት እውነታውን አዛብተው በማቅረብ ሕዝብን ለማደናገር እየሞከሩ ነው::

በመሆኑም፣ ውሸት ሲደጋገም እውነት ሊመስል ይችላል እንዲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል::

በየትኛውም የዓለም ክፍል እንደሚደረገው ሁሉ የሁለት አገሮች ድንበር በዓለም አቀፍ ሕግና በስምምነት የሚወሰን መሆኑ አጠያያቂ አይደለም:: ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር ያላት ድንበርም እ.ኤ.አ በ1902 ዓ.ም እና በ1907 ዓ.ም በወቅቱ በነበረው የኢትዮጵያ መንግሥትና የሱዳን ቅኝ ገዢ በነበረችው በታላቋ ብሪታኒያ መካከል በተደረጉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተወሰነ ሲሆን፣ እነዚህን ስምምነቶች መሠረት በማድረግ ደግሞ እ.ኤ.አ በ1903 እና እ.ኤ.አ. በ1909 ዓ.ም የድንበር ክለላ ተደርጓል::

ይህ ደረጃውን ያልጠበቀ፣ በቂ የወሰን ምልክቶች የሌሉት በመሆኑ ድንበሩ እንደገና እንዲከለል በአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ዘመን ሁለቱ መንግሥታት እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም ስምምነት ተፈራርመዋል:: በዚህ ስምምነት መሠረት በድንበሩ አካባቢ የሰፈራና የእርሻ ሥራን በተመለከተ ዘላቂ መፍትሄ ለማፈላለግ ሁለቱ መንግሥታት ግዴታ ገብተዋል::

ይህንኑ እ.ኤ.አ. በ1972 ዓ.ም የተደረገውን ስምምነት ተፈጻሚ ለማድረግ ሁለቱ መንግሥታት የጋራ የድንበር ኮሚሽን አቋቁመው እንቅስቃሴ ያደረጉ ቢሆንም፣ በ1966 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ በመምጣቱ ጉዳዩ ዕልባት ሳያገኝ ቀርቷል:: የደርግ መንግሥት ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ከላይ የተጠቀሰውን ስምምነት መሠረት በማድረግ የድንበር ጉዳዩ ዕልባት እንዲያገኝ ጥረት ለማድረግ ወስኖ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል:: ከነዚህም ተግባራት የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችን ያካተተ ኮሚቴ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች የያዘ የጥናት ኮሚቴ በማቋቋም

ስለጉዳዩ ጥናቶች እንዲደረጉ የወሰዳቸው እርምጃዎች የሚጠቀሱ ናቸው። በዚሁ የደርግ የስልጣን ዘመን እ.ኤ.አ በ1980 ዓ.ም ደግሞ ካርቱም በተደረገው የሁለቱ አገሮች የሚኒስትሮች መማክርት ኮሚቴ ስብሰባ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዘመን ተቋቁሞ የነበረውን የጋራ የድንበር ኮሚሽን መልሶ ለማዋቀር ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር። በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ በኩል ለኮሚሽኑ የሚያስፈልገውን በጀት እና ስለሚነሱ ጉዳዮች ሰፊ ዝግጅት ተደርጐ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩ ዕልባት ሳያገኝ ደርግ ከስልጣን ወርዷል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ይህንኑ መቋጫ ሳያገኝ የቆየ የድንበር ጉዳይ ወርሷል። ይህንኑ መቋጫ ሳያገኝ የቆየ የድንበር ጉዳይ የኢፌዲሪ መንግሥት በሁለቱ አገሮች መንግሥታትና ሕዝቦች መካከል ዘላቂና አስተማማኝ ግንኙነት ለመመሥረት የሚረዱ በርካታ እርምጃዎችን መውሰዱ ይታወቃል። ከነዚህም ጠቃሚ እርምጃዎች መካከል በቀድሞው መንግሥታት በተፈረሙ ስምምነቶች መሠረት ለድንበሩ ጉዳይ እልባት ለመስጠት የተደረሰው ውሣኔ አንዱ ነው። በዚህም መሠረት ሁለቱ መንግሥታት የጋራ የድንበር ኮሚሽንና በድንበሩ አካባቢ ለተፈጠሩ የዕርሻ መሬትና ሠፈራ ችግሮች መፍትሄ እንዲያቀርብ ኃላፊነት የተሰጠው ልዩ ኮሚቴ እ.ኤ.አ በ2001 ዓ.ም አቋቁመዋል። ይህም እ.ኤ.አ. በ1972 ዓ.ም የተደረገውን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ነው።

የኢፌዲሪ መንግሥት ጉዳዩ የአገራችንን ጥቅም ባስጠበቀና ሕዝብን ባሳተፈ መልኩ እንዲቋጭ ካለው ጽኑ አቋም በመነሳት በጋራ የድንበር ኮሚሽኑና በልዩ ኮሚቴው ውስጥ የሱዳን ተጐራባች የሆኑ ክልሎች በአባልነት እንዲሳተፉ አድርጓል። ኮሚቴዎቹም የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት በቢሮና በመስክ በመገናኘት የተለያዩ ጠቃሚ ተግባራትን ሲያከናወኑ ቆይተዋል።

ከዕርሻ መሬትና ሰፈራ ጋር በተያያዘ ለተከሰቱ ችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ እንዲያቀርብ የተቋቋመው ልዩ ኮሚቴ ንዑስ የመስክ ጥናት ኮሚቴዎችን በማቋቋምና በመስክ በማሰማራት ለችግሮቹ መፍትሄ ለመሻት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በዚህ የድንበር ክፍል የሚገኙ የሁለቱ አገሮች ዜጐች ከይዞታቸው እንዳይፈናቀሉ፣ በዕርሻ መሬት ይገባኛል ጥያቄ ምክንያት ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ የማድረግ ተግባር ተከናወኗል። ይህ ተግባር የተከናወነው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ክልሎች የመስተዳደር አካላት እና አርሶ አደሮች በቀጥታ በማሳተፍ መሆኑ ሚስጥር አይደለም። በዚህ ሂደትም አንድም የኢትዮጵያ አርሶ አደር ከይዞታው እንዳልተፈናቀለ የሚታወቅ ሲሆን፣ በመናፈስ ላይ ያለው አሉባልታ አፀያፊ የሚያደርገው ይኸው እውነታ ነው።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለሱዳን እንደተሰጠ፣ ሁለቱ አገሮች የድንበር ምሰሶ እንዳቆሙና ጉዳዩ እንዳለቀ አድርጐ ማናፈስ ሕዝብን ከመንግሥት እንዲሁም የኢትዮጵያንና የሱዳንን ሕዝቦች ለማጋጨት ያለመ እኩይ ተግባር መሆኑ

ግልጽ ነው። የድንበር ክለላ የራሱ ሕግና ሥርዓት ያለው፣ አንድ መንግሥት እንደፈለገ የሚያደርገው ጉዳይ አለመሆኑ፣ ለእነዚህ ወገኖች የተሰወረ ሆኖ አይደለም። ጠባብ የፖለቲካ አጀንዳን ለማራመድ ሲባል ብቻ እንዲህ አይነት ድርጊት ውስጥ መግባት እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው።

በሁለቱ አገሮች ድንበር አካባቢ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ አፍራሽ ወገኖች ከሚሉት የራቀ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች ጠንቅቀው ያውቁታል። የአካባቢው ነዋሪዎች በቀጥታ እንዲሁም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በሥራው እየተሳተፉ ሲሆን፣ ግልጽ ውይይትም በየጊዜው ተካሄዷል። በመሆኑም ጉዳዩ ከሕዝብ የተደበቀ አስመስሎ ለማቅረብ የሚደረገው ሙከራ መሠረተ ቢስ ብቻ ሳይሆን ተጉራባች በሆኑ የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች መካከል ግጭት ለመፍጠር የታቀደ መሆኑ አያጠራጥርም።

ድንበሩን እንደገና የማካለሉ ተግባር እንደሚናፈሰው ወሬ ያለቀለት ሣይሆን፣ እየተከናወነ ያለው ወደፊት የወሰን ምልክት ለማስቀመጥ የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራን የሚመለከት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እ.ኤ.አ. በ1972 ስምምነት መሠረት የድንበር ማካለሉ እስከሚከናወን ድረስ በአካባቢው የሚገኙ የሁለቱ አገሮች ገበሬዎች በእርሻ መሬት ለመጠቀም እንዲችሉ እየተደረገ ያለው ሥራ አንድም የኢትዮጵያም ሆነ የሱዳን ገበሬ አላፈናቀለም። በመሆኑም፣ እየተናፈሰ ያለው አሳፋሪ አሉባልታ መሠረት የሌለውና ግጭት ለመፍጠር ሆን ተብሎ የሚደረግ አደገኛ አሻጥር መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል።

*ግንቦት 3 ቀን 2000 ዓ.ም.*
*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*
*አዲስ አበባ*